# Ethiopian Civil Service University

Quarterly Magazine
April –June 2024



ኢሲሰዩ በተለያዩ የትምህርት መርሀ-ግብሮች ያሰለጠናቸውን ተማሪዎችን አስመረቀ



ኦሞ አዳራሽ ተመረቀ



*ECSU Research Affairs Directorate Holds the 9th National Conference*

የኢሲሰዩ የከተማ ልማት እና ምህንድስና ኮሌጅ ተመራቂ ተማሪዎች ስልጠና ተሰጠ



# ራዕይ

ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ ፤ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆን

# ተልዕኮ

ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት ፤ በስልጠና ፤ በማማከር ፤ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች በተሟላነት መገንባት

# እሴቶች

ተገልጋይ ተኮር
ልቆ መገኘት
ተባብሮ መሥራት
ሁሌም መማር
ፈጠራን ማበረታታት
ዘለቄታዊ ውጤታማነት
ብዝሃነትን መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

# Table of Contents

ECSU Research Affairs Directorate Holds the 9th National Conference ..........................................1

ECSU Holds a Public Lecture on Ethiopia Entry to BRICS and its Role on Promoting South- South Cooperation: Benefits, Challenges and Prospects..........................................................................................................3

ECSU Holds a Public Lecture on Social Media as Social Glue or Otherwise ..................................................5

ኢሲሰዩ በተለያዩ የትምህርት መርሀ-ግብሮች ያሰለጠናቸውን 2216 ተማሪዎችን አስመረቀ.............................7

ኦሞ አዳራሽ ተመረቀ.....................................................................................9

ኢሲሰዩ ለመካከለኛ የዩኒቨርስቲዉ ሴት አመራሮች የመሪነት ስልጠና ሰጠ...............9

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ እና የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራ ረሙ....................................................................................10

ኢሲሰዩ ለማህበረሰብ ሬዲዮ ጋዜጠኞች እና በጎ ፈቃደኞች ስልጠና ሰጠ..........................11

የኢሲሰዩ የከተማ ልማት እና ምህንድስና ኮሌጅ ተመራቂ ተማሪዎች ስልጠና ተሰጠ.............................12

በከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር የተመራ ከፍተኛ ኃላፊዎች ቡድን በኢሲሰዩ ጉብኝት አደረገ.......................... .................13

ኢሲሰዩ ለከተሞች ፋይናንስ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት ጀመረ....................................................14

ቆይታ ከአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት ጋር.......................................15

# ECSU Research Affairs Directorate Holds the 9th National Conference


Ethiopian Civil Service University (ECSU) Research Affairs Directorate (RAD) held the 9th National Conference with the theme "Public Sector Transformation and Development" from June 3- 4, 2024 at the newly inaugurated Omo Hall. At the conference ESCU scholars, Researchers and invited Guests from Federal Ministries, Universities, and Addis Ababa City Administration participated.




*Professor Fikre Dessalegn, ECSU President*

In his opening speech, Professor Fikre Dessalegn, ECSU President, welcomed the participants of the conference to the momentous academic event of the University and noted that as a successive annual events, the motto of this year conference is "Public Sector Transformation & Development". He also said that this year's gathering, links up the broader agenda of transformation and development and addresses it in the context of Economic development, urban governance, and Public service delivery, Peace and Conflict Management, Diplomacy; and also in the context of Environment and Development; and Human Resource and Leadership Competencies. "ECSU has been actively engaging in research activities for nearly a decade and disseminating its research findings to the end users. Data over the past 9 years indicated that the research productivity in terms of volume of research conducted and the number of publications as articles in journals and proceedings; and also as PhD monographs and other scholarly products are very encouraging. A total of 448 staff grant research topics have been researched, dozens of articles have been published in successive volumes of our journals and proceedings; and also in other local and International journals, and we have records of 109 PhD monographs produced by our alumni. The research productivity is higher when including research outputs by our second degree students. Among these, those published in indexed and journals of wider circulation are obviously a key in enhancing our University's image and visibility at national and global stages, despite five of our journals are still awaiting accreditation by the Ministry of Education." Professor Fikre noted.

He also added that in the past five years alone, ECSU has executed 59 relatively bigger research and consultancy projects, with about 400 million-birr funded by public sector organizations in addition to budget allocated from government treasury and the research findings disseminated and recommendations enabled beneficiaries to deeply understand some of the public sector problems and pin point possible solutions to the problems identified. ECSU is now embarking into the road of becoming Graduate and Research University by maintaining its legacy and responsibility of building public sectors' capacity. Besides, it is gradually evolving as a university of choice by the public servants and employees of private sector, despite the low intake capacity when compared to candidates applying to join our academic programs, Professor Fikre added. Finally he thanked all the researchers for bringing their




*Professor Netsanet Workneh*

expertise and innovative ideas to the conference as well as the organizing committee of the conference.

In her keynote address, Professor Netsanet Workneh,



*Dr. Alemayehu Debebe,*

Vice president of Research and Partnership of Jimma University said that ECSU has been differentiated as Research University based on its achievements and capacities which has shown through its educational programs, innovative researches, initiatives and capacity building efforts. The university's commitment for excellence and advancement of public services for the betterment of the society is exemplary, Professor Netsanet added. She also explained that research and innovations are at the heart of the public service transformation and development. The academic staff is more oriented mostly in teaching rather than research undertakings. In this regard, it is expected to make transformations in mindset, create conducive atmosphere to research and innovation to become research intensive university.

In her inspirational speech Professor Netsanet shared her personal experience to the participants and her determination to get at the position she is now and overcoming the challenges that she was facing in connection to gender stereotype. She also share the experiences of Jimma University on how research works undertake. In jimma University researches and most of international collaborations are initiated by the staffs and holding international conferences and seminars at Jimma University attracted scholars and experts around the world. Nurturing the culture of excellence and innovation, and academic integrity within the university brought positive reputation Professor Netsanet noted. She also underlined the importance of personal growth and development and giving attention to the personal wellbeing in order to be healthy and productive in one's professional life. In his welcoming speech, Dr. Alemayehu Debebe, ECSU Vice President for Research and Partnership, welcomed the participants and noted that ECSU since its establishment passed through several challenges and overcoming these challenges has gained reputation both domestic and international aspects of the academia. Being guided by the principle of continuous learning, it become designated as a Researched University along with the eight first generation universities in the country, Dr. Alemayehu said.

Research universities differ from other universities in its dedication in advancing research culture and wining reputation in research productivity and qualities. Research universities also known to the degree to which their research outcomes enforce the policy making of the nation. We have highly tried to make the consumers of our research outcomes need the information and data of our researches into the policy crafting arena, Dr. Alemayehu noted.

On the conference a total of 42 (16 from outside and 26 from ECSU) research papers were presented. The thematic area distribution of these researches included Economic and development, Urban Governance, Diplomacy, International Relations, Peace, Human Recourse Management, Public Service Delivery, Leadership and Development, and Crosse Cutting Issues.



# ECSU Holds a Public Lecture on Ethiopia Entry to BRICS and its Role on Promoting South- South Cooperation: Benefits, Challenges and Prospects

Ethiopian Civil Service University (ECSU) College of Leadership and Governance, School of Diplomacy and International Relations held a Public lecture under the title "Ethiopia entry to BRICS and its role on promoting south- south cooperation: benefits, challenges and prospects." on May 16, 2024 at ECSU.



Haweni Girma a student at School of Diplomacy and International Relations, warmly welcomed all honorable guests, Ambassadors, academic staffs and students. She noted the academic and work experience of the presenters. Head of School of Diplomacy and International Relations, Dr. Temesegene Aschenek , welcomed the participants and briefed that such kinds of discussion is one of the academicians role at ECSU in the department and also continue in the future. He also introduced the overall objective of joining BRICS in line with Multilateral Diplomacy. The first speaker, Ambassador Evgeny Terekhin, briefly explained the historical formation and development of BRICS. He points out the collective economy of the member states in terms of Group of seven accounts 35.6% of global GDP, while G7 accounts 30.3%. By the end of 2028, the situation will evolve further in BRICS favor: 36.6% versus 27.8%.The formation of BRICS is historically objective as new powerful center of economic growth, financial and political he pointed out. With short period of time BRICS association has rapidly developed and transformed into an extensive multi-level mechanism of interaction on a wide range of issues on the global agenda he underlined. Ambassador Dina Mufti mentioned the overall objective of BRICS. Uplifting and strengthening diplomacy, enhancing development, ensuring peace and security, and enabling south-south cooperation are some of the key objectives. In-line with this mutual respect, sovereign equality and inclusiveness are the fundamental principles of BRICS. Additional new members like Ethiopia, Egypt, Saudi Arabia, Iran, Argentina, and UAE are involving on different section of BRICS such as energy, innovation, environment, science and technology, and trade promotion, he expressed his opinions. Ambassador Dina Mufti highlighted the principle of south-south cooperation. Mutual respect, partnership between equal countries, obtaining benefits evenly, non-interference and joint environment are advocated even if countries like Ethiopia are influenced by some foreign countries by exacerbation of internal problems due to internal vulnerability. Geo political factors such as political, economic, ideological and national character highly impact the foreign powers he added.

The key benefits of BRICS also mentioned by Ambassador Dina. Access to massive market and investors,

boost trade and environment, technological support for education and health sector, access to information for the sector of Medicine and Agriculture are remarked.



Beyond all these benefits political differences, economic inequality, internal problems like corruption, poverty and inequality, overdependence on member states, maintaining independence in foreign relation are articulated as main challenges. Fresh water, oil gas, arable land, fisheries, new organizational capacity and method are the prospects of BRICS to balance the global trade and investment in the near future Ambassador Dina posited.

The participants raised different questions and the presenters were respectively answered the questions. The public lecture was moderated by Dr. Bayisa Tesfaye. Ambassador Dina has graduated with a masters Degree in Political Science and International Relations in Canada and holds a bachelor's degree in political science and international relations from Addis Ababa University. He was prior to his appointment, Dina has been Ethiopia's ambassador to Egypt. He has served as Ethiopia's resident ambassador in Kenya, Sweden, and Zimbabwe and as a non-resident ambassador in many other African and European countries. Mr. Evgeny Terekhin was appointed Ambassador of the Russian Federation to Ethiopia and Representative of the Russian Federation to the African Union and worked as Minister-Counsellor of the Russian embassy to Ethiopia between 2002 and 2006. After several years, returned to Ethiopia as his country's ambassador in 2019. Graduated from the Moscow State Institute of International Relations of the USSR in 1981.



# ECSU Holds a Public Lecture on Social Media as Social Glue or Otherwise

Ethiopian Civil Service University (ECSU) College of Leadership and Governance, Department of Development Communication and Media Studies held a Public lecture under the title " Social Media as Social Glue or otherwise " on May 13 ,2024 at ECSU.

At the opening of the program Dr Lemma Gudissa, Vice President for Academic Affairs, welcomed the participants and expressed his heartfelt gratitude to have Dr Negari Lencho to share his practical and theoretical experience for the University community. ''I am sure ,in the future such kinds of academic activity will pursue in ECSU In light of our unwavering pursuit of academic excellence" he added.



He also briefed the establishment, vision, mission and the new objectives of the university after becoming Research University at national level. ECSU used to provide only under graduate programs during the first few years after its establishment .later on, it broadened its scope of service by launching client oriented programs at post graduate levels. Since then the university has been diversifying its postgraduate programs to address divers' demands of the country's civil service. Currently, the university has three colleges, one school and institute: offering 26 post graduate programs, 9 PhD programs, and 11 under graduate programs in different modalities he underscored.

At the beginning of the lecture Dr. Negari Lencho thanked the organizer of the public lecture and explained the benefit of creating discussion form among the scholars. Well-functioning democracy requires free and diverse platform capable of keeping people informed, holding powerful actors to account and enabling public discussion on public affairs. So this public lecture could create discussion form among the academician he added.

He also stated that digital media environments are changing in part as a result of technological and market developments largely associated with the rise of digital technology. So Social media helps society to keep connected with each other. People also use different networking for communication, promote business, advertising, product campaign, getting news updates and share an opinion. Because of such reasons social media has so many positive sides that change people's lives positively and also so many drawbacks .So People should aware of the advantages and disadvantages of social media and try to use it more responsibly to minimize the risks.

He also briefed that social media is cheap and easily accessed and digital revolution changes citizen from audience to producer in the technological era and

this unique feature has contributed to a sense of participation and personal engagement among the users. As a result, peoples critically select message and media responsibly and also government should play its role. In conclusion, Dr. Negari remarks the biggest social media dilemma could face to stay up-to-date with constant changing world and democracy. The intersection of social media and the rule of law, democracy and fundamental rights, with a particular focus on hate speech, disinformation and media pluralism should be studied further to reduce its effect on a country. Department of Development Communication and Media Studies head, lecturers, students, staff and invited guests participated. Different questions and comments were raised for the presenter and he respectively answered them. The public lecture was moderated by Dr. Waqgari ,Dr Gemechisa and Dr Zeleke. At last, Dr. Gebre Miruts, College of Leadership and Governance Dean, thanked all the participants and the organizers for their effective coordination. Negari Lencho has PhD in Journalism &Mass Communication, Chairperson of a Standing Committee on Human Resource Development, Labor & Technology Affairs of the FDRE House of Peoples Representatives.

In addition he was Minister of FDRE Government Communication, Head of Oromia Communication Bureau and Assistant Prof. and Dean, School of Journalism and Communication, Addis Ababa University.



Dr. Lemma Gudissa,
Vice President for Academic Affairs,



# ኢሲሰዩ በተለያዩ የትምህርት መርሀ-ግብሮች ያሰለጠናቸውን 2216 ተማሪዎችን አስመረቀ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በ2016 ዓ.ም በተለያዩ መርሀ-ግብሮች ያሰለጠናቸውን 2216 ተማሪዎችን ሰኔ 29 ቀን 2016 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው ዋና ጊቢ በድምቀት አስመረቀ። ተመራቂዎቹም 122 በመጀመሪያ ዲግሪ፣ 2119 በሁለተኛ ዲግሪ እና 27 ደግሞ በፒኤች ዲ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ ናቸው።



የዕለቱ የክብር እንግዳ ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ የዴሞክራሲ ማዕከል ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ ሰብሳቢ ለተመራቂ ተማሪዎች ባስተላለፉት መልዕክት፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ምስረታ፣ ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ጉዞና ከፌዴራሊዝም ስርዓት አጀማመር ጋር ጠንካራ ቁርጠኝት ያለው መሆኑን፣ ዩኒቨርሲቲው ከምስረታው ጀምሮ ባለው ጉዞው ከሰባ ሺህ በላይ ምሩቃንን በማፍራት እና ምሩቃኑም በከፍተኛ የመንግስት የኃላፊነት በታዎች ላይ ተሰማርተው መንግስትና ሕዝብ የሰጣቸውን ኃላፊነቶች እየተወጡ መሆናቸውን ገልጸዋል። አስከትለውም የሲቪል ሰርቪሱ ያሉበትን መሰረታዊ ስብራቶች ለመጠገንና ዘመናዊ፣ ነጻና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት መንግስት የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ መሆኑን የገለጹት ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሲቪል ሰርቪሱን አቅም የመገንባት ተልዕኮ የተሰጠው ተቋም እንደመሆኑ መጠን፣ ይህን ተልዕኮውን ለመወጣት በትጋት እየሰራ ያለ ስለሆነ፣ ተቋማዊና አስተዳደራዊ መዋቅር የሚያስፈልገው መሆኑን በማመንና፣ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን ዕቅድን መሰረት ያደረገ የሽግግር ሥራዎችን እያሰራ እንደሚገኝ አመልክተው፣ የስራ አመራር ቦርዶም ይህ ጉዞ እንዲሳካአስፈላጊውንክትትልናድጋፍእንደሚያደርግገልጸዋል። ለዕለቱ ተመራቂዎችም ባስተላለፉት መልዕክት፣ ተመራቂዎች በዩኒቨርሲቲው በነበራቸው ቆይታ ያካበቱትን ዕውቀትና ክህሎት በሚሰማሩበት የስራ መስክ ሀገሪቷንና ኅብረተሰቡን በታማኝነትና በታታሪነት፣ ከአድልኦና ከሙስና በጸዳ፣ ሰብዐዊነትን በተላበሰ መልኩ ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት፣ የመልካም አስተዳደር



ችግር እንዲቃለል የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ለተመራቂ ተማሪዎች ባስተላለፉት መልዕክት፣ በብርቱ ጥረትና ትጋት በየትምህርት ፕሮግራሞቹ የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚገባ



በማጠናቀቅ ህልማችሁን ዕውን ለማድረግ በመቻላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል፡፡ በማስከተልም፣ ዩኒቨርሲቲው በእስካሁኑ ጉዞው ከ70 ሺህ በላይ ተማሪዎችን ከዲፕሎማ እስከ ፒኤች ዲ ዲግሪ ድረስ አስተምሮ ማስመረቅ የቻለ መሆኑንና ከእነዚህም መካከል 700 የሚሆኑት የጎረቤት ሀገራት ፐብሊክ ሰርቫንቶች መሆናቸውንገልጸው፣ይህምለሀገራችንኩራትመሆኑንተናግረዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በትምህርት ሚኒስቴር ስር እንዲደራጅ በመንግስት በመወሰኑእናበሀገራችንካሉትየመጀመሪያትውልድዩኒቨርሲቲዎች ጋር በድህረ ምረቃና ምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ምድብ መመደብ መቻሉ፣ የሀገራችንን ሲቪል ሰርቪስ አቅምና ብቃት የመገንባት ተልዕኮውን ለመወጣት ጠንካራ መንፈስና ተነሳሽነት የፈጠረለት መሆኑን የገለጹት ፕሮፌሰር ፍቅሬ በ2016 ዓ.ም ከመንግስት በተመደበው 837 ሚሊዮን ብርና ከባለድርሻ አካላት በተገኘ ድጋፍ በርካታ የትምህርት፣ የምርምርና ማማከር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች የተከናወኑ እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችምለመንግስትሰራተኞችየተሰጡመሆናቸውንገልጸዋል፡፡



ዩኒቨርሲቲው ከጊዜ ወደ ጊዜ ተወዳዳሪነቱና ተመራጭነቱ እያደገ በመምጣቱም በ2016 ዓ.ም 7268 ተማሪዎችን ተቀብሎ ሲያስተምር የቆየ ሲሆን፣ ለ2017 የትምህርት ዘመን ወደ 7000 የሚጠጉ የማስተርስና የፒኤችዲ ተወዳዳሪዎችን በመለየት ብሔራዊ የድህረ-ምረቃ መግቢያ ፈተና እንዲወስዱ ዝርዝራቸው ለትምህርት ሚኒስቴር መላኩን አመልክተዋል፡፡ ፕሮፌሰር ፍቅሬ በንግግራቸው ዩኒቨርሲቲው ብቁና በቂ የአካዳሚክ ሰራተኞች እንዲኖሩት በርካታ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን አብራርተው 31 አዳዲስ የትምርት ፕሮግራሞችም ቀረጻ ስራ መጀመሩን ተናግረዋል፡፡ የፐብሊክ ሴክተሩን አቅም ከመገንባት አኳያም በ2016 ዓ.ም ከ3206 በላይ ስልጠናና የምዘና ስራ መከናወኑንም አክለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ላለፉት ሶስት አሰርት ዓመታት የሀገራችንን ሲቪል ሰርቪስ የሰው ኃይል በማልማትና በመንግስት የተዘረጉ የሪፎርም ፕሮግራሞችን ትግበራ




በማማከር፣ ሴክተሩ ለሀገር ግንባታ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱንም ፕሮፌሰር ፍቅሬ ገልጸዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በምርምር ሥራዎች ላይ በሚያደርገው ትኩረት በማሳደግ በ2016 ዓ.ም በ5 ሚሊዮን ብር በጀት 49 ምርምሮችን ያካሄደሲሆን፣ባለፉትአምስትተከታታይአመታትበአጠቃላይ497 ችግርፈቺናለፖሊሲግብዐትየሚሆኑምርምሮችመሰራታቸውንም ፕሮፌሰርፍቅሬገልጸዋል፡፡ዩኒቨርሲቲውየተሟላራስገዝዩኒቨርሲቲ እንዲሆን በመንግስት በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከ2016 በጀት ዓመት ጀምሮ በሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ የሽግግር ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን የገለጹት ፕሮፌሰር ፍቅሬ፣ ትምህርትና ስኬት የህይወት ዘመን ጉዞ አካል ቀጣይ በመሆናቸው፣ በቀጣዩ የሥራ ዓለም ተመራቂዎች የበለጠ አቅማቸውን በመገንባት ሀገራችንን ከድህነት ለማውጣት የሚደረገውን ጥረት በሙሉ ኃየላቸው መደገፍ እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

# ኦሞ አዳራሽ ተመረቀ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በአካዳሚክ ሕንጻ የሚገኘዉ ኦሞ አዳራሽ በኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ግንቦት 26/2016 ዓ.ም የክብር እንግዳ ፕ/ር ነጻነት ወርቅነህ የጅማ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ትብብር ም/ፕሬዚዳንት ፣ የኢሲሰዩ ም/ፕሬዚዳንቶች ፣ ከተለያዩ ተቋማት የመጡ ተመራማሪዎች እና የዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ አባላት በተገኙበት ተመረቀ፡፡





አዳራሹ በተለያዩ ዘመናዊ እና የተደራጀ ቁሳቁስ የተሟላ ሲሆን ለስልጠናዎች ፣ሴሚናር ፣ወርክሾፕ ለተለያዩ ኩነቶች አመቺ ሲሆን በጠቅላላዉ ስባት መቶ ሀምሳ ታዳሚያንን በአንድ ግዜ የመያዝ አቅም አለዉ፡፡

# ኢሲሰዩ ለመካከለኛ የዩኒቨርስቲዉ ሴት አመራሮች የመሪነት ስልጠና ሰጠ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ የሰራተኞች ድልድል መዋቅር መሰረት ወደ መካከለኛ አመራርነት ለመጡ 37 ሴት አመራሮች ከግንቦት 7 ቀን 2016 ዓ/ም ጀምሮ ለ ሁለት ቀናት የቆየ ስልጠና ሰጠ፡፡



በስልጠናው ላይ የተሳተፉት በአካዳሚ፣ በምርምርና በአስተዳደር ዘረፍ የተመደቡ ሴት አመራሮች ሲሆኑ፣ ስልጠናው "የላቀ የአመራርነት ክሂልን ማስጨበጥ" በሚል ርዕስ ላይ የሚያተኩር መሆኑን፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች አካትቶ ትግበራ ስራ አስፈጻሚ አቶ ዝናቤ ታደሰ ገልጸዋል፡፡ የስልጠናው ይዘት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የአመራርነት ሚና ላላቸው ኃላፊዎች የሚሰጥ ሲሆን ይዘቱም የስራ አመራርን ምንነት፣ የመሪን ሚና፣ የመሪነትን ምንነት፣ የመሪነትን ፍኖተ ካርታ፣ የመሪነትን ክህሎት፣ የአመራር ዘይቤዎች፣ መሪነትበስርዓተጾታውስጥእናየስሜትብልህነትበሚሉዋናዋና ርዕሶች የተዘጋጀ መሆኑን ስልጠናውን የሰጡት በዩኒቨርሲቲው የህዝብ ስራ አመራር መምህር ዶ/ር ተመስገን ዳኜ ገልጸዋል፡፡ አሰልጣኙ እንደገለጹት የስልጠናው መርሃ ግብር በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች አካትቶ ትግበራ ስራ አስፈጻሚ በኩል ስለተዘጋጀ ለሴቶች ብቻ ቢሰጥም፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከመካከለኝ ደረጃ በላይ ለሚገኙ የስራ ኃላፊዎች የሚጠቅም ስልጠና መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ እና የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር ጋር በጋራ በመተባበር የአመራሩን አቅም አገልግሎት አሰጣጡን በሚያዘምኑ ጉዳዮች ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

በፊርማ ስነስርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል



ከንቲባ አቶ ጃንጥራር አባይ፣ የየካ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ብርሀኑ ረታ፣ የየካ ክ/ከተማ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ሃላፊ አቶ መገርሳ ገላና፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የምርምርና ትብብር ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር አለማየሁ ደበበ እና የአካዳሚ ስታፍ ምሁራን እንዲሁም የክ/ከተማ እና የወረዳ አመራሮች ተገኝተዋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራር አባይ እንደገለፁት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ከዚህ ቀደም ብዙ ምሁራንን ያፈራ ስመ ጥር ተቋም መሆኑን ገልፀው የካ ክ/ከተማም እያከናወናቸው ካሉ የተለያዩ የልማት ስራዎች ጎን በአገልግሎት አሰጣጥም ስመ ጥር ተቋም ለመሆን ለአመራሩ እና ባለሙያዎች ገንቢ ስልጠናዎችን ለመስጠት ከተቋሙ ጋር መስራቱ ተገቢ መሆኑን አመራሩም ስልጠናውን በአግባቡ ሰልጥኖ ለለውጥ እንዲሰራ አሳስበዋል።

የየካ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ብርሀኑ ረታ በፕሮግራሙ ላይ ለተገኙ እንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክታቸውን አስተላለፈው ይህ የአቅም ግንባታ ስልጠና እውን እንዲሆን የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ድጋፍ በማድረጉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። አቶ ብርሀኑ አያይዘውም በቀጣይ በተለያዩ ጊዜያት ከወረዳ ጀምሮ ላሉ አመራሮች ዩኒቨርሲቲው ገንቢ ስልጠናዎችን እንደሚሰጥ እና በሁለቱ ተቋማት ያሉ ግንኙነቶች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልፀዋል። የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ትብብር ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር አለማየሁ ደበበ ፕሮግራሙን ላመቻቹ አካላት በሙሉ ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ሰላሳ አመታት የትውልድ አቅም ግንባታ በማሳደግ በተለያዩ ስራ ዘርፎች ባለሙያዎች እያፈራ እንደሚገኝ ገልፀው በቀጣይ ለክ/ከተማው አመራሮች አቅም የሚሰጡ የተለያዩ ስልጠናዎችን እንደሚሰጥ ገልፀዋል። በእለቱ ከሳጥን ውጪ ማሰብ እና ቀና አመለካከት በሚል እርእስ በዶ/ር ታምሩ ፈይሳ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ችሎታዎችን ለማወቅ ከሳጥን ውጭ ማሰብ ያለው



ጠቀሜታ፣ችግሮችን ለመፍታት በተለየ መልኩ የማሰብ ጥበብ እንዲሁም ከተለመዱ አሰራሮች ወጣ ብሎ በማየት የተሻሉ ውጤታማ አሰራሮችን ማምጣት እና ቀና አመለካከት በስራ ላይ ያለው ፋይዳ የሚሉ ሃሳቦች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በቀጣይ በጋራ የአመራሩን አቅም በሚያጎለብቱና የአገልግሎት አሰጣጡን በሚያዘምኑ ጉዳዮች ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል። ምንጭ፡- የካ ኮሙኒኬሽን



# ኢሲሰዩ ለማህበረሰብ ሬዲዮ ጋዜጠኞች እና በጎ ፈቃደኞች ስልጠና ሰጠ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ምርምር እና ትብብር ምክትል ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት ከመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ጋር በመተባበር፣ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ሬዲዮ FM 100.5 ለሚሰሩ ጋዜጠኞች እና በጎ ፈቃደኞች ግንቦት 29 ቀን 2016 ዓ/ም የአንድ ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጠ።



ስልጠናውን ያደራጁት የሬዲዮ ጣቢያው ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ ምህረት ካሳ ሲሆኑ፣ በስልጠናው የተሳተፉት ሙያተኞች፣ በጎ ፍቃደኞችን ጨምሮ አስር የሚዲያ ባለሙያዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፤ የስልጠናውን ዓላማ ሲያስረዱ "ስልጠናው የተዘጋጀው የመገናኛ ብዙሀንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ፣ የጥላቻ ንግግርን እና የሀሰተኛ መረጃን ስርጭትን ለመቆጣጠር በወጡት ሁለት አዋጆች ላይ ሰራተኞቻችንግንዛቤእንዲጨብጡለማስቻልነው" ብለዋል። ስልጠናውን የሰጡት ከመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የመጡ ሁለት የስራ ኃላፊዎች ሲሆኑ፣ የመገናኛ ብዙሃን ሚና፣ ዓለም ዓቀፍ ህጎች፣ የኢፌድሪ ህገ መንግስት፣ የመገናኛ ብዙሃን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የጥላቻ ንግግርን እና ሀሰተኛ መረጃ ማሰራጨትን ለመቆጣጠር የወጡ ሁለት አዋጆች ላይ ትኩረት ያደረገ ስለጠና ሰጥተዋል።



በመጨረሻም የመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ላደረገው ቀና ትብብር ምርምር እና ትብብር ምክትል ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት ልዩ ረዳት ወ/ሮ መሰረት በቀለ አማካኝነት የምስጋና





ደብዳቤ ተሰጥቷል። ወ/ሮ ምህረት ካሳም በመጨረሻ ባደረጉት ንግግር ለባለስልጣኑ እና ለአሰልጣኞቹ ያላቸውን ልባዊ ምስጋና አቅርበው፣ ሬዲዮ ጣቢያው ጥራት ያለው መረጃ ለማህበረሰቡ ማቅረብ እንዲችል፣ "በፋክት ቼክ" ላይ ያለውን ክፍተት የሚዘጋ ስልጠና በባለስልጣኑ በኩል እንዲያዘጋጅላቸው ጠይቀዋል።

# ለኢሲሰዩ የከተማ ልማት እና ምህንድስና ኮሌጅ ተመራቂ  ተማሪዎች ስልጠና ተሰጠ

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ልማትና ምህንድስና ኮሌጅ ጋር በመተባበር፣ በዶክትሬት እና በማስተርስ ዲግሪ ትምህርታቸውን ላጠናቀቁ ተመራቂ ተማሪዎች፣ ለሁለት ቀናት ሲሰጥ የቆየው ስልጠና ተጠናቀቀ።



የስልጠናው መርሃ-ግብር ሰኔ 24 እና ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ/ም በዩኒቨርሲቲው ህዳሴ አዳራሽ የተካሄደ ሲሆን በስልጣናው ላይ የተሳተፉት፣ በከተማ ልማት እና ምህንድስና ኮሌጅ ትምህርታቸውን የተከታተሉ አምስት እጩ ዶክተሮች እና አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ የማስተርስ ዲግሪ ተመራቂዎች መሆናቸውን፣ በኢሲሰዩ የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ደጉ በቀለ አስታውቀዋል።ስልጠናው ሲጀመር የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚንስትር ዴኤታ አቶ ፈንታ ደጀን ባደረጉት ንግግር፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስር ዋና ዋና ተግባራት ላይ አጠር ያለ ገለጻ አድርገዋል። አቶ ፈንታ አስከትለውም “እናንተም ሄዳችሁ ከተማ ላይ የምታገኟቸው እነዚህን ዋና ዋና ፒላሮች ነው። ስራው በባህሪው ቅንጅትን የሚፈልግ፣ በአግባቡ ካልተመራ ለስኬት የማይበቃ፣ ለሀገር እና ለህዝብ፣ በተለይም ለከተማ ነዋሪዎች የሚጠበቀውን ፋይዳ የማያስገኝ መሆኑን በመገንዘብ በተጨማሪም ለስራው ስኬት የማይተካ ሚና በመጫዎት የሚጠበቅባችሁን ሁሉ እንድታደርጉ አደራ እላለሁ።” በማለት ስልጠናውን ከፍተዋል።



የስልጠናው ይዘት፣ የኢትዮጵያ ከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ረቂቅ ፖሊሲ፣ የከተማ ልማት ረቂቅ ፖሊሲ፣ የአላማ መር ፕሮጀክት ልማት እስትራቴጂ፣ የስማርት ሲቲ እስራቴጂ፣ ፓርትነርሽፕ ልማት እና ከንቲባዊ ስራ አመራር በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው። በአምስቱ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስልጠናውን የሰጡት በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ፣ የፖሊሲ እና እስትራቴጂ የምርምር ተንታኝ የሆኑት ዶ/ር አበባየሁ ሙሉጌታ እና ዶ/ር አማን አሰፋ ሲሆኑ፣ ከንቲባዊ አመራር በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ደግሞ፣ በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የኢትዮጵያ ከንቲባዊ አመራር ኢኒሼቲብስ አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር ያሬድ ተሾመ ናቸው። በመዝጊያው ስነ-ስርዓት ላይ የተገኙት፣ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ ባደረጉት ንግግር የከተማ ስራ አመራር በብዙ ተግዳሮት የተሞላ መሆኑን ገልጸው፣ በተግዳሮቱ ሳይዋጥ ለውጥ የሚያመጣ አመራር ሌጋሲውን አስቀምጦ ማለፍ እንደሚችል አብራርተዋል። ክብርት ሚንስትሯ በማስከተልም “ከምትመረቁበት ቀን አንስታችሁ፣ እኔ ለከተማዬ ለውጥ ማምጣት አለብኝ በማለት እንደ ኮኮብ ማብራት አለባችሁ ። ከተማ ያያል ይሰማል፤ አያየንም ብለን የምንሰራው ስራ ፍጻሜው አያምርም ። በከተማችን ሌጋሲያችንን አስቀምጠን ለማለፍ ንጹህ እጅ ያስፈልገናል።” በማለት መንግስት በከተሞች ላይ የሚከተለውን ፖሊሲ እና አስትራቴጂ ለማስፈጸም ቁርጠኛ መሆንን ይጠይቃል ብለዋል።





# በከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር የተመራ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ቡድን በኢሲሰዩ ጉብኝት አደረገ

የከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር በክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ የተመራና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን ያካተተ ቡድን ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮችና ከከተማ ልማትና ምህንድስና ኮሌጅ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አደረጉ። ሰኔ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ክብርት ሚኒስትሯ በዩኒቨርሲቲው ባደረጉት ጉብኝት ወቅት በተደረገው በዚሁ ውይይት ላይም በዩኒቨርሲቲውና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መካከል ያለውን ነባር ትብብር የበለጠ ለማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በስፋት ተወያይተዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ በውይይቱ ላይ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በሀገሪቱ ብቸኛ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆኑን በማስታወስ በርካታ ሥራዎችን ያከናወነ እና ተልዕኮውምን በብቃት ሲወጣ የቆየ ተቋም መሆኑን ገልጸዋል። በከተማ ልማት



ዘርፍም ዩኒቨርሲቲው ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደ ትልቅ አጋር በመሆን የዘርፉን ባለሙያዎች አቅም ለማሳደግ በርካታ ስራዎችን ሲያከናውን የቆየና አሁንም በስፋት እየሰራ ያለ ተቋም መሆኑን የጠቀሱት ፕ/ር ፍቅሬ አሁን ካለው የከተሞች በከፍተኛ ደረጃ የመስፋፋት ዝንባሌ ጋር ተያይዞ ከሚስተዋለው በፕላን የመመራት ችግር ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያግዙ አዳዲስ የትምህርት መርሀ-ግብሮችን በመቅረጽ እና ነባር ፕሮግራሞችንም በመከለስ ሂደት ላይ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር አብሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው ለዚህም ዩኒቨርሲቲው ያለውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል። በውይይቱ ላይ የከተማ ልማትና ምህንድስና ኮሌጅ ዲን ዶ/ር ደጉ በቀለ ባደረጉት አጭር ገለጻ ኮሌጁ ከምስረታው ጀምሮ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው በርካታ ተማሪዎችንም በመደበኛው የትምህርት መርሀ-ግብር አሰልጥኖ ከከፍተኛ ዲፕሎማ እስከ ፒኤች ዲ ድረስ ሊያስመርቅ የቻለ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪም በሚሰጡት የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችም እና የማማከር ስራዎችም ከሁለት መቶ ሺ በላይ ለሚሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መሰጠት መቻሉንና ለተለያዩ ከተሞችም የከተማ መሪ ፕላኖችን መስራት እና የማሻሻያ ስራዎችን ከማከናወንም ባሻገር በርካታ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችም መከናወናቸውን ዶ/ር ደጉ ገልጸዋል። ዶ/ር ደጉ በገለጻቸውም ኮሌጁ ያሉት የትምህርት ፕሮግራሞች ያሉባቸውን ክፍተቶች መለየትና ክለሳ ማድረግ፣ ከከተሜነት መስፋፋትና ዕድገት ጋር ተያይዞ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞችን መቅረጽ፣ በኮሌጁ ያሉትን መምህራን አቅም ማሳደግ፣ የሚሰጡት ስልጠናዎችም ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ማስቻል፣ ልዩ ልዩ ልምዶችን በመቀመር አጋርነትንና ትብብር የበለጠ ማጠናከር በወደፊት የትኩረት አቅጣጫነት ተለይተው የተያዙና በዕቅድ ተይዘው እየተሰራባቸው መሆኑን አመላክተዋል። ክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ የከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው በእስካሁኑ ጉዞው በሀገር ደረጃ ትልቅ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያለ ተቋም መሆኑ በመግለጽ በአሁኑ ወቅት የሚስተዋለው ከፍተኛ የከተሜነት መስፋፋት ጋር ተያይዞ እየመጡ ያሉ ከፍተኛ ፍላጎቶች፣ ስማርት ከተሞችን ቀድሞ የማዘጋጀትና በአግባቡ መምራት እንዲሁም በመሰሰሉት ጉዳዮች ላይ የዩኒቨርሲቲው እገዛ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ረገድ በጋራ በምንሳራቸው ጉዳዮች መለየትና እንዴት እንደሚሰሩም መመካከር አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው በዚህ ረገድም ቀጣይ ውይይቶችን ማድረግ እና ያለውን ግንኙነትም የበለጠ ማጠናከር አስፈላጊ ነው ብለዋል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያደርገው ሁሉን አቀፍ የልማት እንቅስቃሴም የዩኒቨርሲቲው ምሁራን ያላቸው የካበተ ልምድና እስካሁንም በሀገር አቀፍ ደረጃ ያበረከቱት አስተዋጽኦ የላቀ መሆኑን አስታውሰው በቀጣይም ከዩኒቨርሲቲው እገዛ ለተቋሙ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል። በመጨረሻም ክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ በዩኒቨርሲቲው የሚገኘውን የከተማ ልማትና ምህንድስና ኮሌጅ ቤተ-ሙከራን



እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ያሉትን የመሰረተ ልማቶች ተዘዋውረው የጎበኙ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው እያከናወናቸው ባሉት ሥራዎችም ያላቸውን አድናቆት ገልጸዋል።

# ኢሲሰዩ ለከተሞች ፋይናንስ ባለሙያዎች ስልጠና ሰጠ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ስልጠና ኢንስቲትዩት ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለመጡ ለከተማ ፍይናንስ ዘርፍ ባለሙያዎች የአርባ አምስት ቀናት ስልጠና ሰጠ ፡፡



በ ስ ል ጠ ና ው መክፈቻ መርሀ-ግብር ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የስልጠና ኢኒስቲቲውት ዲን አዜብ አስፋ (ዶ/ር) እንዳሉት የከተሞች ፋይናንስ ስልጠና እና ምዘና በሃገራችን ለመጀመሪያ ግዜ የሚሰጥ እንደመሆኑ በዚህም ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ እንዲሰጥ በመደረጉ ትልቅ ደስታ ይሰማናል ፡፡ ኢሲሰዩ ከሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተለየ መልኩ በአጫጭር ግዜ ስልጠና ፣በምርምር፣በማማከር እንዲሁም በትምህርት ከመጀመሪ ዲግሪ እስከ 3ኛ ዲግሪ በመስጠት የሲቪል ሰርቫንቱን አቅም ላለፉት 29አመታት እየገነባ ያለ ተቋም ነዉ ብለዋል፡፡በዚህም ስልጠና ቆይታችሁ በከተማ ፋይናንስ ዙሪያ ብቁ ባለሙያ ሆናችሁ እንደምትወጡ ሙሉ እምነት አለኝ ብለዋል፡፡"የከተማ ችግር መፍታት ከየትም አይመጣም ከእናንተ ከባለሙያዎች እንጂ ልምዳችሁን አቅማችሁን በስልጠና በመደገፍ ወደ ትግበራ መለወጥ ፣ችግራችን ከከአይምሮአችን በላይ ስለማይሆን ቁርጠኝነት ብቻ ነዉ ከኛ የሚጠበቅብን " ብለዋል፡፡ የከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የከተሞች ገቢ ሪፎርም ፕሮጀክት ዋና ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ዜኒት ኢብራሂም በበኩላቸው ባደረጉት ንግግረ እስካሁን ባለው ሁኔታ በከተሞቻችን የከተሞች ፋይናንስ በጥናት በህግና በስረአት እየተመራ አይደለም ፡፡ አሁን ላይ ተቋማችን የከተሞች ፋይናስ ስረአትን በሁሉም ክልሎች ወጥ እና በህግና በስረአት የሚመራ ለማድረግ ከተሞች ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩ የዘመነ የፋይናንስ ስረአት እንዲኖራቸው ማድረግ ዋንኛ ግባችን ነዉ፡፡ ሰልጣኞችም ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ 100 የመጀመሪያ ሰልጣኞች እንደሆኑ፣ ለ45 ቀናት በተግባር እና በፁሁፍ የተደገፈ ስልጠና እንደሚወስዱ በማጠቃለያዉም የመውጫ ፈተና እንዳለ ገልጸዋል ፡፡ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የከተሞች እድገት በየአመቱ 4.5% ሲሆን ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ 22% በከተሞች የሚኖር ነው አሁን ላይ በኢትዮጵያ 117 ከተሞች ሲኖሩ የኢትጵያ ከተሞች ከአጠቃላይ በጀታቸው 24% ብቻ የሚሸፍኑ ሲሆን ሌላዉ በጀታቸው በመንግስት የሚደጎምመሆኑን ጠቁመዋል፡ ፡የከተሞችን የፋይናንስ ስረአት በማዘመን በህግ በስረአት እና በእውቀት የሚመሩ እንደ ሃገር ወጥ የሆነ የፋይናንስ ስረአት ያላቸው ለማድረግ የከተማ መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም ስራ አስፈጻሚዋ እንደሉት ስልጠናውን በተገቢው መንገድ እንድትከታተሉ ከስልጠናውም በኋላ በከተሞች ፋይናንስ ላይ በቂ እውቀት እንዲኖራችሁ እውቀታችሁን ለስራ ባልደረቦቻችሁ በማካፈል የከተሞችን ገቢ በማሳደግ ሂደት ላይ የመጀመሪያ ሰልጣኞች እንደመሆናችሁ አወንታዊ ሚና እንጠብቃለን ብለዋል፡፡



# ቆይታ

## ከአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት ጋር

**የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች መዋቅር መሰረት ሰራተኞችን ለመደልደል የድልድል መርሀ- ግብር ነድፎ ወደ ሥራ በመግባት የድልድል ስራውን በቅርቡ ማጠናቀቁ ይታወቃል። ከዚህ የምደባ ስራ ጋር ተያይዞ የምደባ ኮሚቴው ያከናወናቸውን ሥራዎችና አጠቃላይ ሂደቱን አስመልክቶ ከዶ/ር ታዴዎስ ሜንታ የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ ም/ል ፕሬዚደንት ጋር ያደረግነው ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው ቀርቧል። መልካም ቆይታ።**

**ዓ/አ/ህ/ግንኙነት፡ በዩኒቨርሲቲው አዲስ መዋቅር መሰረት በአስተዳደር የስራ መደቦች ላይ ሰራተኞችን የመደልደል ሥራ በቅርቡ መጠናቀቁ ይታወቃል። እስቲ ድልድሉ ከመካሄዱ በፊት የተደረጉት ቅድመ-ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ?**

**ዶ/ር ታዴዎስ፡** በመጀመሪያ በአካዳሚክ አመራር ነው ምደባ የጀመርነው። አካዳሚክ ማለት የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዘዳንት እና የምርምርና ትብብር ምክትል ፕሬዘደንት ዘርፎችን ያካትታል። በእነዚህ ውስጥ ሰባ አራት የኃላፊነት የስራ መደቦች ላይ በሚመለከታቸው ዘርፎች ውድድር ተደርጎ አመራሮች እንዲመደቡ ተደርጓል።

ከዚያ በኋላ ነው የአስተዳደር እና ማኔጅመንት ዘርፎች ውድድር እና ድልድል የቀጠለው። ይሄ ውድድርና ድልድል ሙሉ በሙሉ የተካሄደው በአስተዳደር እና ልማት ምክትል ፕሬዚደንት ሰብሳቢነት፣ ዩኒቨርሲቲው ባቋቋመው ኮሚቴ አማካኝነት ነው ። ድልድሉም የተፈጸመው፣ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን መጋቢት 859 /2014 ዓ/ም በሚል በወጣው በአዲሱ የስራ ድልድል መመሪያ መሰረት እና እሱን ለማስፈጸም በ2014 እና 2015 ዓ/ም የወጡ ሰርኩላሮችን በመከተል ነው። በ2015 ዓ/ም የወጣው 859 /2014ን በመጠኑ አሻሽሎ የወጣ ሰርኩላር ስለሆነ፣ በዋናነት ይህንኑ ተጠቅመናል፤ በተጨማሪም ሌሎች በ2014 ዓ/ም ላይ የወጡ ሰርኩላሮች ስለነበሩ፣ እነዚህን መነሻ በማድረግ፣ አጠቃላይ የድልድል ሂደቱን ጀምረናል።

የድልድል ሂደቱን ስንጀምር ፣ ዩኒቨርሲቲያችን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ስለሆነ፣ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የምርምር ዩኒቨርሲቲ መዋቅር ከመጣልን በኋላ፣ መዋቅሩን መነሻ በማድረግ፣ ከተቋቋመው ኮሚቴ ጋር ውይይት አድርገናል፡ ፡ ውይይታችን ያተኮረው፣ አሰራራችንን ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ለማድረግ የምንችልበትን አቅጣጫ መከተል እንዳለብን ነው። ይህም ተግባራዊ እንዲሆን፣ ለሰራተኞቻችን ግልጽ እና ሊታዩ በሚችሉበት ስፍራ መመሪያዎቹን፣ ሰርኩላሮቹን እና መዋቅሩን ጭምር እንዲለጠፍ አድርገናል። ይህንን ሂደት ካለፍን በኋላ ከሰራተኞች ጋር ውይይት በማድረግ፣ መመሪያውን እንዲያውቁ እና አስፈላጊ ጥያቄ ካለ እንያዲነሱ በማድረግ፣ የማወዳደር እና የመደልደል ስራው ቀጥለናል።

**ዓ/አ/ህ/ግንኙነት፡ የድልድል ሂደቱስ ምን ይመስላል? በዝርዝር ቢያስረዱን።**

**ዶ/ር ታዴዎስ፡** የድልድል ስራው ሂደት ቅድም እንደገለጽኩት የድልድል መመሪያው እና ሌሎች ሰርኩላሮች ለሰራተኞች እንዲታዩ ለጥፈን፣ ሰራተኞችም ጊዜ ወስደው እንዲያነቡት እና ጥያቄ ካላቸውም እንዲዘጋጁ እድል ሰጥተናል፤ በተጨማሪም ከሁሉም የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር ግማሽ ቀን በመውሰድ፣ ሰፋ ያለ ውይይት አድርገናል። በዚህም ውይይት የመመሪያውን ሀሳብ እንዲረዱ በመመሪያው ላይ ሰፊ ገለጻ አድርገናል፤ ላነሷቸው ጥቄዎችም በአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዘደንት በኩል አስፈላጊውን ማብራሪያ ሰጥተናል። መዋቅሩን በተመለከተ፣ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተላከውን የስራ መደብ በሙሉ በመዘርዘር፣ በብቃት እና የሰው ሀብት አስተዳደር ስራ አስፈጻሚ በኩል ገለጻ ተደርጓል።

ይህንን መነሻ በማድረግ የተነሱ ጥያቄዎችን እና ሰራተኛው እንዴት መወዳደር አለበት? በምን ያህል መደብ ላይ መወዳደር ይችላል? ለውድድር የሚያበቁ ነገሮችስ ምንድን ናቸው? ሰራተኞችስ ምን ምን ሊኖራቸው

ይገባል? የሚከለከሉ ነገሮች ምንድን ናቸው? የሚለውን በሙሉ ለሰራተኞቻችን በማብራራት ሂደቱን ጀምረናል። በመቀጠል በተለይ የስራ ልምድ በሚጠይቁ ስራ መደቦች ላይ ግልጽ አረዳድ ለመያዝ እንዲያስችል፣ በምዝገባ ወቅት ቀጥታ የስራ ልምድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ለመወዳደር ምን ምን የስራ ልምድ ሊኖራቸው እንደሚገባ፣ በሚመዘገቡበት ጊዜ ለውድድር ሊያበቃቸው የሚችል የትምህርት ዝግጅት የትኛው እንደሆነ በመወያየት እና ግልጽ በማድረግ ፣ ኮሚቴው ኃላፊነት ወስዶ እያንዳንዱን የተሰጠንን መደብ እንደገና በማየት፣ ለእያንዳንዱ የስራ መደብ ቀጥታ የስራ ልምድ የተባሉትን በሙሉ ለይቶ ለማኔጅመንቱ በማቅረብ አስተያየት አሰጥተናል። አስተያየት ከተሰጠበት በኋላም እንደገና ማሻሻያ በማድረግ መልሰን ለማኔጅመንቱ በማቅረብእንዲወሰን አድርገናል። ከዚህ በኋላ በተደረገው ማሻሻያ ላይ እንደገና ለሰራተኛው ገለጻ ተደርጎ፣ ቀጥታ የስራ ልምዶች በሚባሉት ላይ ግልጽ አረዳድ እንዲኖር አድርናል፤ በተጨማሪም በማኔጅመንት የጸደቀው እና በኮሚቴየተፈረመው ለሰራተኛው በሚታይ ቦታ እንዲለጠፍ ተደርጎ፣ በዚሁ መሰረት የውድድር ምዝገባው ተካሂዷል ።



*ዶ/ር ታዴዎስ ሜንታ*
*የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ ም/ል ፕሬዚደንት*

ቅደም ተከተሉን በተመለከተም፣ መመሪው የአመራር መደቦች ቅድሚያ ሊሰሩ እንደሚገባቸው ስለሚያስቀምጥ፣ ቡድን መሪ እና ከዚያ በላይ ያሉ የስራ መደቦች ላይ ለብቻ ምዝገባ የሚፈጽሙ ሰዎችን አደራጅተን፣ ለብቻ እንዲመዘገቡ አድርገናል። እነዚህ በአስተዳደርና ልማት የሚገኙ የስራ መደቦች ሃምሳ ዘጠኝ ሲሆኑ፣ ለውድድር የተመዘገቡት፣ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ናቸው። በቀጣይም ኮሚቴው ሰነዶቹን በአግባቡ እና በጥንቃቄ ካጣራ በኋላ፣ ለውድድር የሚበቁትን ለፈተና እንዲዘጋጁ በማድረግ፣ የኒቨርሲቲው ፈተና በማውጣት ረገድ ያለውን ከፍተኛ ልምድ ተጠቅሞ ያወጣውን ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል።

**ዓ/አ/ህ/ግንኙነት፡የድልድል ሂደት የወሰደው ጊዜ በዕቅድ ተይዞለት ከነበረው የጊዜ ሰሌዳ በእጅጉ የዘገየ ነበር፡ ፡ ለዚህ ተጠቃሽ የሆኑት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?**

**ዶ/ር ታዴዎስ፡** በአጠቃላይ የውድድሩ እና ድልድሉ ሂደት፣ አንድ አመት የሚሆን ጊዜ ወስዷል፤ እንዲህ ለመዘግየቱ እንደምክንያት የሚጠቀሱት በርካታ ቢሆኑም፣ ዋና ዋና ከሚባሉት ጥቂቶቹን መጥቀስ አስፈላጊ ነው። አንደኛ፣ ሰራተኞች ሲመዘገቡ የተማሩት ትምህርት እና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተፈላጊ ችሎታዎች ተብለው የተካተቱት ትምህርቶችአንዳንዶቹአይጣጣሙምነበር።የተሰጠንአቅጣጫ እያንዳንዱ ሰው ሲመዘገብ ትምህርቱ ቀጥታ በሲቪል ሰርቪስ የተጠቀሰው ብቻ መሆን አለበት የሚል ስለነበረ፣ ለተወሰነ ጊዜ ለመመዝገብ ተቸግረናል። በአመራር የስራ መደቦች ላይ የጎላ ችግር አላጋጠመንም፤ ተወዳድረው ላለፉት ከሐምሌ 1 ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ የምደባ ደብዳቤ እንዲያገኙ አድርገናል።

የቁጥራቸው አነስተኛ መሆን፣ መካተት የሚገባውን የስራ

ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመነጋገር እያካተትን ስራውን ለማቀላጠፍ እገዛ አድርጎልናል፡፡

ወደ ባለሙያ የስራ መደቦች ስንመጣ፣ በተለይም ከደረጃ ስምንት በታች ባሉት የስራ መደቦች ላይ፣ ምዝገባ ሲካሄድ፣ ከተጠየቁት የትምህርት ዝግጅቶች ውስጥ፣ አንዳንዶቹ አልተካተቱም፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የተካተቱት በተለያየ ስም ነበር፡፡ ለምሳሌ በአንዳንድ መደቦች አካውንቲንግ ይጠይቃሉ፤ ግን አካውንቲንግ ኤንድ ፋይናንስን አይጠይቁም፤ ስለዚህ አካውንቲንግ ከጠየቀ አካውንቲንግ ኤንድ ፋይናንስ ለምን አልጠየቀም? የሚል በጣም ሰፋ ያለ ችግር ነበረ፤ ይሄንን ለመፍታት እና አካውንቲንግ ለሚጠይቅ የስራ መደብ አካውንቲንግ ኤንድ ፋይናንስ መካተት አለበት ፤ በሚለው ላይ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር መግባባት ላይ ለመድረስ፣ በተደጋጋሚ መጻጻፍን ጠይቆናል፡፡

በተመሳሳይ በጥገናና እና በምህንድስና ስራ አስፈጻሚ ውስጥ ያሉት በርካታ የትምህርት መስኮች፣ አንዱ ለአንዱ መያዝ አለበት የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ መመሪያው ግልጽ አካሄዶች ስላልነበሩት እና ግልጽ ባልሆኑት ላይ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመነጋገር ማስተካከልን እንደ አማራጭ ስለሚያስቀምጥ፣ ሰራተኛን ከመጥቀም አኳያ ብዙ ትምህርቶች እንዲካተቱ እየጠየቅን፣ ኮሚሽኑ ያመነበትን መሰረት አድርገን፣ ብዙ ትምህርቶች እንዲካተቱ አድርገናል፡፡ ከዚህ አኳያ ስራውን ስንጀምር ከተላኩልን ተፈላጊ ችሎታ አንጻር ያልተካተቱ ትምህርቶችን ለማካተት እንዲቻል ለማድረግ የሄድንበት ርቀት ውስብስብ እና አድካሚ ነበር፡፡ እንግዲህ በዋናነት ለመዘግየቱ ዋና ዋና ከሚባሉት ምክንያቶች አንዱ ይሄ ነበረ፡፡

ሁለተኛው ሰራተኞች ሲመዘገቡ፣ በተለይ ፕሮፋይል ሲደራጅ፣ ቀጥታ የስራ ልምድ የተሰላበት መንገድ፣ አንዳንዱን ስንመለከት የድምር ስህተት ነበረ፤ የተያዙ የስራ ልምዶች ተገቢ ያልነበሩ ናቸው፤ የፍትሀዊነት ጥያቄ ስለሆነ፣ አንዳንዶቹ መቀነስ ወይም መስተካከል ነበረባቸው፤ ስለዚህ እነዚህን እርምጃዎች ለመውሰድ ኮሚቴው፣ ወደ አንድ ሽህ የሚደርሰውን የሰራተኛ ፕሮፋይል እንደገና ማየት ነበረበት፡፡ ይህንንም በማድረጋችን፣ የስራ ልምድ ያልሆኑ ግን እንደስራ ልምድ የተያዙትን ማስወጣት ወይም የስራ ልምድ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገር ግን እንደስራ ልምድ ያልተያዙትን ማካተት ነበረበት፡፡ የተፈጠረው የስሌት ችግር መስተካከልም ነበረበት፤ እናም ኮሚቴው እነዚህን ሁሉ ተግባራት ለማከናወን ባደረገው ጥረት ነው ረጅም ጊዜ ሊወስድ የቻለው፡፡

ይህንን በማድረጋችን በሰው ሀብት አካባቢ የተቋቋመው ኮሚቴ በመመዝገብ ሂደት ላይ ችግሮች ስለነበሩበት ለማስተካከል እድል አግኝተናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለቀጥታ የስራ ልምድ የተሰጠውን ልዩ ትኩረት ሙሉ በሙሉ እንደገና ማየታችን፣ ከምደባ በኋላ ሊመጣ የሚችለውን መካሰስ እና አላግባብ ተመደበ የሚል ጥያቄ ማስቀረት እንድንችል እድል ፈጥሮልናል፡፡ ይሁንና ይህንን ለማጠናቀቅ እና ስራውን ለማጥራት የሄድንበት አካሄድ ብዙ ጊዜ ወስዶብናል፡፡ በጠቅላላው ለድልድሉ ረዘም ያለ ጊዜ መውሰድ ዋና ዋና ምክንያት የሆኑት እነዚህ ናቸው፡፡

**ዓ/አ/ህ/ግንኙነት: *ለድልድሉ መዘግየት በምክንያትነት ከተጠቀሱት አንዱ የሰራተኞችን መረጃ በአዲስ መልክ ማደራጀት እንደነበር ገልጸውልናል፡፡ ነገር ግን ይህ ሥራ በዋናነት መከናወን የነበረበት በሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ኮሚቴው ወደዚህ ስራ የገባበት እና ሥራውን ሊያዘገይ የቻለበት አስገዳጅ ምክንያት ምንድን ነው ?***

***ዶ/ር ታዴዎስ:*** ኮሚቴው ማህደር የማጥራቱን ስራ የሰራበት ዋናው ምክንያት ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ተዛማጅ ስራዎች ሁሉ እንደስራ ልምድ ይያዙ ነበር፤ ሌላው ቀርቶ የድልድል መመሪያው 859/2014 በሰርኩላር ተስተካክሎ ነው እንጂ መጀመሪያ በነበረው ተዛማጅ የስራ ልምድ እንደሚያዝ ወስኖ ነበረ፤ በኋላ ግን በሰርኩላር ቀጥታ የስራ ልምድ ብሎ ስላስተካከለው ያንን እንደገና መስራት አስፈልጓል፡፡ የሰው ሀብት በፊት በነበረው የአሰራር ልማድ ሰርቶ ማምጣቱ፣ በኮሚቴው ላይ ተጨማሪ ስራ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፤ ኮሚቴውም አስቀድሞ ይህንን የማጣራት ስራ ለመስራት የተገደደው ቆይቶ ቅሬታ እንዳይነሳ ለማድረግ የጠራ አሰራር እንዲኖር በማስፈለጉ ነው፡፡ ሌላው እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው፣ በሂደቱ አንዳንድ ሀሰተኛ ማስረጃዎችንም ለማግኘት አስችሎናል፡፡

**ዓ/አ/ህ/ግንኙነት: *በኮሌጆች ላይ ተመድበው ይሰሩ የነበሩ የአስተዳደር ሰራተኞች የስራ ልምዳችን ተጥሎብናል የሚል ቅሬታ አላቸው በዚህ ምን ምላሽ አለዎት?***

***ዶ/ር ታዴዎስ:*** ኮሌጆች አካባቢ የነበሩ የአስተዳደር ሰራተኞች አግባብነት ያለው የስራ ልምድ አልተጣለባቸውም፡፡ የአስተዳደር ሰራተኞችን የስራ ልምድ በተለያዩ የስራ ክፍሎች ውስጥ አካተናል፤ ለምሳሌ በለውጥ ስራ አስፈጻሚ፣ በአሉሙናይ እና በሌሎችም የስራ ክፍሎች ውስጥ በበርካታ የስራ መደቦች ላይ እንዲወዳደሩ አድርገናል፡፡ እነሱ የነበሩበት የስራ መደብ በአሁኑ መዋቅር ሙሉ በሙሉ ቢፈርስም፣ ኮሚቴው የስራ መዘርዝራቸውን መሰረት አድርጎ፣ ከነበረባቸው ኋላፊነት አኳያ የት ይመደቡ በሚል በተለያዩ መደቦች ላይ እንዲመደቡ አድርጓል፤ ሆኖም በአንዳንድ ቡድን መሪ እና ባለሙያ አራት የመሳሰሉ ከፍተኛ የስራ መደቦች ላይ ያመለከቱት ማግኘት ያልቻሉት የትምህርት ዝግጅታቸው

ከስራ ልምዳቸው ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ ነው። ከዚህ ባለፈ ዩኒቨርሲቲው የሰራተኞቹን ጉዳይ በጥልቀት ተመልክቶ፣ የአስተዳደር ሰራተኛ የስራ ልምድ በሚጠይቅ የስራ መደብ ላይ በሙሉ፣ የእነሱን የስራ ልምድ ታሳቢ በማድረግ፣ ረዳት አስተዳደር ሰራተኛ በሚል የስራ ልምዳቸው እንዲካተት አድርጓል። ከላይ እንደገለጽኩት ችግሩ የአስተዳደር የስራ ልምድ ይዘው የትምህርት ዝግጅታቸው ለአስተዳደር የስራ መደብ የማይጋብዛቸው ሰራተኞች ባመለከቱበት መደብ ላይ ሳይመደቡ የቀሩ ይኖራሉ።

**ዓ/አ/ሀ/ግንኙነት፡ በዚህ ድልድል በአጠቃላይ ስንት ሰራተኞች መደብ አግኝተዋል?**

**ዶ/ር ታዴዎስ**፡ መመሪያው በመጀመሪያ ያስቀመጠው አካሄድ "ሰራተኛው ተወዳድሮ ያግኝ" ስለሚል፣ ዩኒቨርሲቲው ባወጣው የድልድል ማስታወቂያ፣ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ቀጥታ የስራ ልምዳቸውን እና የትምህርት ዝግጅታቸውን አቅርበው የውድድሩን መስፈርት አሟልተው ተወዳድረው ያሸነፉ 469 ሰራተኞች መደብ አግኝተዋል።

ሁለተኛው አካሄድ ሰራተኛው በተወዳደረባቸው በሁለቱም የስራ መደቦች ካላገኘ፣ በተለይም ዲፕሎማ እና ከዚያ በታች ከሆነ እየሰራ ያለበት መደብ በሌላ ተወዳዳሪ ካልተያዘ እዚያው ላይ ይመደብ የሚል ነው፤ ሶስተኛው ተመጣጣኝ መደብ በኮሚቴው ይሰጠው እና ይመደብ የሚል ነው፤ አራተኛው ተመጣጣኝ መደብ ከሌለ ፈቃደኛነቱ ተጠይቆ ዝቅ ባለ መደብ ላይ ይመደብ የሚል ነው፤ አምስተኛው አማራጭ ሰራተኛው የትምህርት ዝግጅቱን አሟልቶ የስራ ልምዱ አንድ አመት እና ከዚያ በታች ከቀረው በታው ክፍት ከሆነ በታው በታሳቢነት ይሰጠው የሚል ነው፤ ከዚህ ውጪ ከሆነ ሰራተኛውን ማንሳፈፍ ግዴታችን ነው።

እንግዲህ ከላይ ተወዳድረው አሸንፈው ከተመደቡት በተጨማሪ የተዘረዘሩትን የመመሪያውን አማራጮች ተጠቅመን 372 ሰራተኞችን መድበናል፤ እንዲሁም አንድ አመት እና ከዚያ በታች የስራ ልምድ የቀራቸው 11 ሰራተኞች ምደባ እንዲያገኙ አድርገናል፤ መደቡ ከፍ ብሎ የሚጠይቀው መስፈርትም እንደዚሁ ከፍ ብሎ የመጡ መደቦች ላይ ያሉትን ሰራተኞች፣ ከፍተኛ የስራ ልምድ ይዘው ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው በመሆናቸው ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመነጋገር ከፍ ያለውን መስፈርት ዝቅ አድርገውልን ወደ 61 የሚሆኑ ሰራተኞችን መመደብ ችለናል። ይህ የሚያሳየው ዩኒቨርሲቲው በተቻለው መጠን ምንም ሰው እንዳይንሳፈፍ ለማድረግ ያደረገውን ጥረት ነው። ሌላው 11 ሀኪሞች በታቸው የመደብ ለውጥ አድርጎ ስለመጣ በጤና ጥበቃ መስፈርት መሰረት የመደብ ለውጥ እንዲያገኙ አድርገናል። በድምሩ 924 ሰራተኞች በድልድሉ ምደባ ያገኙ ናቸው።

**ዓ/አ/ሀ/ግንኙነት፡ በዚህ ድልድል ምደባ ያላገኙ የአይቲ ሰራተኞች መኖራቸው ይታወቃል፤ የእነዚህ ሰራተኞች ዕጣ ፈንታስ ምንድነው?**

**ዶ/ር ታዴዎስ**፡ በዚህ ዙሪያ ሰራተኞቹን የሚያሰጋቸው ምንም ችግር የለም፤ ነገር ግን እነሱን ለመመደብ አብዛኛው በስራ አስፈጻሚው የመጡት የስራ መደቦች ከሙያቸው አንጻር ተተንትነው የመጡ ናቸው። ለሁሉም ሰራተኞች በቂ የሆነ የስራ መደብ ቢኖረንም፣ የትኛው የትምህርት ዝግጅት ለየትኛው የስራ መደብ ይመጥናል የሚለውን በገለልተኛ ሙያተኛ ማሳየት ስላለብን ነው ምደባቸው የዘገየው። አሁን ምደባ ያላገኙት የአይቲ ሙያተኞች አምስት ናቸው የአምስቱንም ፕሮፋይል በባለሙያ አሳተን በሚቀርብልን ሙያዊ አስተያየት መሰረት በቅርቡ ምደባ ያገኛሉ።

**ዓ/አ/ሀ/ግንኙነት፡ በመጨረሻ መግለጽ የሚፈልጉት ነገር ካለ ቢያስተላልፉልን።**

**ዶ/ር ታዴዎስ**

በመጨረሻ የማስተላለፈው መልእክት፣ ይህ ድልድል የተካሄደው ከዩኒቨርሲቲው ሪፎርም ጋር በተያያዘ ስለሆነ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ሰራተኛ በተመደበበት የስራ መደብ ላይ አቅሙን አሟጦ በመስራት ለሪፎርሙ መሳካት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

**ዓ/አ/ሀ/ግንኙነት፡** ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ለዚህ ቃለ መጠይቅ ስለተባበሩን በአለም አቀፍ እና ህዝብ ግንኙነት ስራ አሰፈጻሚ ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን::

**ዶ/ርታዴዎስ፡**

እኔም አመሰግናለሁ።

# የ2016ዓ.ም የተማሪዎች ምረቃ በዓል በፎቶ



















Ethiopian Civil Service University
Committed to Excellence in the Public Sector

Contact Address:
Hot line: +251-116-46-30-15
Tel.0116 46 2887
Fax: 0116463016
P.O.Box5648
E-mail: IPRD@ecsu.edu.et
Pr.ecsu@gmail.com
Website: www.ecsu.edu.et
Tweeter: @ECSU tweets
FM Radio:-100.5MHz
Facebook: Ethiopian Civil Service University